መመሪያ ቁጥር 924/2014

# የማኅበረሰብ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን አገልግሎት መመሪያ

የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን

# መመሪያ ቁጥር 924/2014
# የማኅበረሰብ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን አገልግሎት መመሪያ

የመገናኛ ብዙሃን ሙሉ በሙሉ ባልተስፋፋባቸው ወይም የማኅበረሰቡን የዕለት ተለት ጉዳዮች የሚሸፍኑ መገናኛ ብዙሃን በሌሉባቸው የአገራችን አካባቢዎች ለማኅበረሰቡ ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት የሚሠራጩ የማኅበረሰብ ሬዲዮንና ቴሌቪዥን አገልግሎቶችን ማስፋፋት፤ ለማኅበረሰቡ ወቅታዊ መረጃ በማቅረብ፣ በማስተማር እና በማዝናናት ፈጣንና ቀጣይነት ላለው ሁለንተናዊ ዕድገት ቁልፍ የሆነውን በመረጃ የበለፀገ ሕብረተሰብ በመፍጠር በአገራችን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት መሆኑን በማመን፤

አገራችን የበርካታ ብሔረሰቦች አገር በመሆኗ፤ የአገራችንን ልዩ ልዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጥቅም መሠረት ያደረገ፣ ብዝሃነቱ የተረጋገጠ፣ ጥራቱን የጠበቀ፣ ተደራሽና ቀጣይነት ያለው የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት እንዲስፋፋ ልዩ ትኩረት በመስጠት መንቀሳቀስ የዜጎችን መረጃ የማግኘት መብት በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀፅ 30 መሰረት በማኅበረሰብ የብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ለመሠማራት የማኅበረሰብ ብሮድካስት ፈቃድ ማግኘት በማስፈለጉና ፈቃድ አሰጣጥ ሒደቱን ግልፅ፣ ፍትሐዊ፣ አሳታፊ እና የሃሳብና የመረጃ ብዝሃነትን የሚያስፋፋ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 6(1)፣(5) እና 31(1)(መ)፣(2)፤ መሰረት የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ በመስጠት መገናኛ ብዙሃንን ማስፋፋት እና ባለፈቃዶችም የሙያዊ ሥነ-ምግባር፣ ሕገ መንግስቱን፣ የአገሪቱን ሕጎች እንዲሁም፤ የሕዝብን ሰላም፣ ደኅንነት፣ የዜጎችን ተነፃፃሪ መብቶችና ጥቅሞች ባከበረ መልኩ በኃላፊነት ስሜት ሥራቸውን ማከናወናቸውን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 12(7) እና አንቀጽ 90(2) መሰረት ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ቦርድ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት መመሪያ ቁጥር 924/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ ***"የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት"*** ማለት በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበር አማካኝነት የተቋቋመ፤ ባለቤትነቱና አስተዳደሩ

በማኅበረሰቡ ተወካዮችና ፍላጐት የሚመራ፣ የፕሮግራም ትኩረቱን በማህበረሰቡ ጉዳዮች ላይ ያደረገ፣ በፕሮግራም ዝግጅትና መረጣ የማኅበረሰቡን ተሳትፎ መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ፣ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን አገልግሎት ነው፡፡

2/ **"ማኅበረሰብ"** ማለት በአንድ አካባቢ በመኖራቸው ወይም የተለየ ማንነት በመጋራታቸው የተነሳ፣ የተለየ የጋራ ፍላጎትና ዓላማ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ወይም በተለየ የጋራ ፍላጎትና ዓላማ ዙሪያ የተሰባሰበ የሕዝብ ክፍል ነው፤

3/ **"ማኅበር"** ማለት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት በኢትዮጵያውያን የተመሰረተ፣ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ሲሆን ፆታን፣ ዕድሜን፣ ሙያን ወይም የጋራ ፍላጎትን መሰረት አድርገው የተቋቋሙ ማኅበራትን የሚያካትት ነው።

4/ **"የብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት ከምድር ወደ አየር፣ በኬብል ወይም በሳተላይት ማሰራጫዎች አማካኝነት አጠቃላይ ሕዝብን ወይም የተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍልን ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት በድምጽ ወይም በምስል ወይም በድምጽና በምስል ያለክፍያ የሚተላለፍ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን አገልግሎት ነው፡፡

5/ **"የፈቃድ አመልካች"** ማለት የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን ቅፅ ሞልቶ ያመለከተ የማኅበረሰቡ ሕጋዊ ተወካይ ነው፤

6/ **"የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃድ"** ማለት በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት ከባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሲሆን፤ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ በማግኘት አገልግሎት የሚሰጥ አካልንም ይጨምራል፡፡

7/ **"ከምድር ወደ አየር የሚሠራጭ የብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት የሬዲዮ ሞገድ በመጠቀም የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡

8/ **"የሳተላይት ብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት በሳተላይት ማሰራጫዎች አማካይነት የሚሠራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ነው፡፡

9/ **"አካባቢያዊ ስርጭት"** ማለት ከክልል በታች ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ተወስኖ፤ በማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚሰራጭ የብሮድካስት አገልግሎት ስርጭት ነው፡፡

10/ **"መልክአ ምድራዊ የማኅበረሰብ ብሮድካስት"** ማለት መልክአ ምድራዊ ወሰንን መሠረት በማድረግ ከአሰፋፈር አኳያ በአንድ በተወሰነ አካባቢ ለሚኖሩ ማኅበረሰቦች አገልግሎት የሚሰጥ የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ነው፡፡

11/ **"የጋራ ፍላጎት የማኅበረሰብ ብሮድካስት"** ማለት ፆታን፣ እድሜን፣ ሙያን ወይም መሰል የጋራ ወይም ተመሳሳይ ፍላጐትን መሰረት አድርገው በሚመለከተው መንግስታዊ አካል በመመዝገብ በሕግ የሰውነት መብት ለተሰጣቸው ለትርፍ ያልተቋቋሙ ማህበር አባላት አገልግሎት የሚሰጥ የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ነው።

12/ **"የከፍተኛ ትምህርት ተቋም"** ማለት ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር፣ ለክልል ትምህርት ቢሮ ወይም አግባብ ላለው ሚኒስቴር ወይም ቢሮ የሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ነው።

13/ **"የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የማኅበረሰብ ብሮድካስት"** ማለት በከፍተኛ የትምህርት ተቋም የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ እገዛ የሚያደርግ እና ለተቋሙ ማኅበረሰብ ብቻ አገልግሎት የሚሰጥ የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ነው።

14/ **"ማኅበረሰብ ተኮር የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ብሮድካስት"** ማለት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋም እና በተቋሙ አካባቢ ለሚገኙ ማኅበረሰቦች አገልግሎት የሚሰጥ የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ነው።

15/ **"ማኅበረሰብ ተኮር የአካባቢ አስተዳደር ብሮድካስት"** ማለት በአካባቢው አስተዳደር እና ማኅበረሰብ የተቋቋመ እና ለአካባቢው ማኅበረሰብ አገልግሎት የሚሰጥ የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ነው።

16/ **"ልዩ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት"** ማለት በአካባቢው የማኅበረሰብ ክፍሎች የተቋቋመ፤ የፕሮግራም ትኩረቱን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ብቻ አድርጎ ለአካባቢው ማኅበረሰብ የብሮድካስት አገልግሎት የሚሰጥ፤ በሳተላይት አማካኝነት የሚሠራጭ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ሲሆን፤ የልጆች ፕሮግራም ቻናልን፣ የዜና ፕሮግራም ቻናልንና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

17/ **"ለአጭር ጊዜ የሚሠጥ የማኅበረሰብ ብሮድካስት"** ማለት አገልግሎቱን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ለመስጠት ታቅዶ የተቋቋመ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ነው፡፡

18/ **"መደበኛ የማኅበረሰብ ብሮድካስት"** ማለት አገልግሎቱን ላልተወሰነ ጊዜ በመደበኛነት የሚሠጥ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ነው፡፡

19/ **"የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል"** ማለት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብን ማመልከቻ ተቀብሎ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች መሟላታቸውን በማጣራት የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ በባለሥልጣኑ ውስጥ የተቋቋመ መደበኛ የሥራ ክፍል ነው፡፡

20/ **"ፕሮግራም ኃላፊ"** ማለት በብሮድካስት አገልግሎት ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ያለው የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

21/ **"የሕዝብ ጥቅም"** ማለት ከግል ወይም ከጥቂት ቡድኖች የጥቅም ፍላጎት በተቃራኒ የማኅበረሰቡን የደኅንነት፣ የምጣኔ ሃብት፣ የባሕል፣ የፖለቲካ እና መሰል ተፈጥሮ ያላቸውን ጥቅሞች ጨምሮ የሰፊው ሕዝብ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡

22/ **"የአካባቢ አስተዳደር"** ማለት የማኅበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ በሚቋቋምበት አካባቢ የሚገኝ መዘጋጃ ቤት፣ ዞን፣ ልዩ ዞን፣ ወረዳ ወይም ልዩ ወረዳ ማለት ነው።

23/ **"የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ"** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

24/ **"ባለሥልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ነው፡፡

25/ **"ቦርድ"** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ቦርድ ነው፡፡

26/ **"አዋጅ"** ማለት የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 ነው፡፡

27/ **"ተባባሪ ፕሮግራም አዘጋጅ"** ማለት ማንኛውም የሀገር ውስጥ የሚዲያ ፕሮግራም በማዘጋጀት ወይም የውጭ አገር የብሮድካስት ፕሮግራም በአገር ውስጥ የብሮድካስት አገልግሎት አማካኝነት ለማሰራጨት ከማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሰረት ፕሮግራሙን ፈቃድ ባለው የብሮድካስት አገልግሎት አማካኝነት የሚሰራጭለት ሰው ነው፡፡

28/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

29/ ሌሎች በአዋጁ የተሰጡ ትርጉሞች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

30/ በወንድ ጾታ የተገለጸው አገላለጽ የሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ ወይም በአዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀፅ 3(1) እና (3) መሠረት በሌሎች ሃገራት የተቋቋሙና በኢትዮጵያ ላይ አተኩረው በሚሰሩ ከምድር ወደ አየር፣ በኬብል ወይም በሳተላይት አማካኝነት በሚሰራጭ የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. <u>የመመሪያው መርሆች</u>

ይህ መመሪያ በሚከተሉት መርሆዎች የሚመራ ይሆናል፡-

1/ የሕዝብ ጥቅምን መሠረት ያደረጉ፣ ለአካባቢ የማኅበረሰብ ክፍሎችና ማኅበረሰባዊ ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት የሚሰጡ፣ ብዝሃነትንና አገራዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎቶችን በሁሉም የአገራችን ክፍል ማስፋፋት፡፡

2/ መገናኛ ብዙሃን ባልተስፋፋባቸው የአገራችን አካባቢዎች የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የመረጃ ተደራሽ ማድረግ፡፡

3/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ሠጪዎችን ሁለንተናዊ አቅም በማሳደግ ቀጣይነታቸውን ማረጋገጥ፡፡

4/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዶች የሙያውን ሥነ-ምግባር፣ ሕገመንግስቱን፣ የአገሪቱን ሕጎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅምን አክብረው መስራታቸውን ማረጋገጥ፡፡

# ክፍል ሁለት
# የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አይነቶችና አደረጃጀት

## 5. የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት አይነቶች

1/ የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት አይነቶችና አደረጃጀቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) መልክአ ምድራዊ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት፣

ለ) የጋራ ፍላጎት የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት፣

ሐ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት፣

መ) ማኅበረሰብ ተኮር የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ብሮድካስት አገልግሎት፣

ሠ) ማኅበረሰብ ተኮር የአካባቢ አስተዳደር ብሮድካስት አገልግሎት፣

ረ) ልዩ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት እና

ሰ) ባለሥልጣኑ በየጊዜው እያጠና የሚወስናቸው ሌሎች የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎቶች፡፡

2/ ባለፈቃዱ የአደረጃጀት ለውጥ ማድረግ ሲያስፈልገው በማንኛውም ጊዜ ለባለሥልጣኑ በማመልከት ፈቃድ ሲያገኝ አደረጃጀቱን ሊቀይር ይችላል፡፡

## 6. የማኅበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያዎች አደረጃጀት እና የበጀት ምንጭ

1/ ማንኛውም የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ በሚከተለው ተቋማዊ አደረጃጀት ይደራጃል፡-

ሀ) በአካባቢው ማኅበረሰብ ተወካዮች የሚመሰረት ጠቅላላ ጉባኤ፣

ለ) በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ 7 አባላት ያሉት ቦርድ፣

ሐ) የጣቢያው ሥራ አስኪያጅ፣

መ) የፕሮግራም ኃላፊ

ሠ) የበጎ ፈቃደኞች ማስተባበሪያ ክፍል፣

ረ) የቴክኒክ ክፍል፣ እና

ሰ) ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች፡፡

2/ የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ የበጀት ምንጭ ከማህበረሰቡ አባላት መዋጮ፣ ከማስታወቂያ፣ ከስፖንሰርሽፕ፣ ከለጋሾችና ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚገኝ ሲሆን፣ የገንዘብ ምንጩ ከሕጋዊ አካል በሕግ አግባብ የተገኘ መሆን አለበት፡፡

## 7. የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ጠቅላላ ጉባኤ አደረጃጀት

1/ ማንኛውም የማኅበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ ሰብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢ እና ፀሀፊ ያለው የራሱ ጠቅላላ ጉባኤ ሊኖረው ይገባል።

2/ ጠቅላላ ጉባኤው ሁሉንም የማኅበረሰቡን አባላት በማካተት ይደራጃል፤ ሁሉንም የማኅበረሰቡን አባላት ለማካተት ካልተቻለ በሚከተለው ቁጥርና ሁኔታ ይደራጃል፡-

ሀ) መልክአ ምድራዊ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ ወይም ማኅበረሰብ ተኮር የአካባቢ አስተዳደር ብሮድካስት ጣቢያ ወይም ልዩ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ ከሆነ፤ ቢያንስ 150 በሆኑ ከአካባቢው ማኅበረሰብ፣ ከብዙሃን ማኅበራት፣ ከአስተዳደር ምክር ቤት፣ በቁጥር አነስተኛ ከሆኑ የማሕበረሰቡ ክፍሎች፣ ከትምህርት ተቋማት እና ከሌሎች የማኅበረሰቡ ክፍሎች በፍትሐዊነት በተወከሉ አባላት ይመሠረታል።

ለ) የጋራ ፍላጎት የማኅበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ ከሆነ፤ ቢያንስ 150 በሆኑ የጋራ ፍላጎት ማህበሩ አባላት እና ከማኅበረሰቡ የተለያዩ አካላት በፍትሐዊነት በተወከሉ አባላት ይመሠረታል።

ሐ) ማኅበረሰብ ተኮር የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ብሮድካስት ጣቢያ ወይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የማኅበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ ከሆነ፤ ቢያንስ 200 በሆኑ ከተቋሙ ተማሪዎች፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ አመራር፣ መምህራን፣ ሠራተኞች እና ከተማሪዎች ህብረት አመራር፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ፣ ማኅበራት፣ አስተዳደር ምክር ቤት እና ከሌሎች የማኅበረሰቡ ክፍሎች በፍትሐዊነት በተወከሉ አባላት ይመሠረታል።

## 8. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ እና ሥልጣን እና ተግባር

1/ ጠቅላላ ጉባኤው በዓመት ቢያንስ 1 ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም አስቸኳይ ጉዳይ ሲኖር በጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ ወይም በጠቅላላ ጉባኤ አንድ ሦስተኛ በሚሆኑ አባላት ወይም በቦርዱ ጠያቂነት በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

2/ ጠቅላላ ጉባኤው የብሮድካስት ጣቢያው የበላይ አካል ሲሆን የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) የማኅበሩን መመስረቻ ፅሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ያፀድቃል፤ ያሻሽላል፣

ለ) የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይሰይማል፣

ሐ) የጣቢያውን የቦርድ አባላት ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት መካከል ይመርጣል፣ ቦርዱም ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ በመምረጥ ለጠቅላላ ጉባኤው ያሳውቃል፡፡

መ) የተጓደሉ የጠቅላላ ጉባኤ እና የቦርድ አባላት እንዲሟሉ ያደርጋል፣

ሠ) በቦርዱ የሚቀርብለትን አመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርት እና በጀት ይገመግማል፤ ያፀድቃል፣

ረ) የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ፣ የምርጫ፣ የድምፅ፣ የውሳኔ አሰጣጥ እና የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ሥልጣን እና ተግባር እንዲሁም ለመሰል ጉዳዮች የሥነ ሥርአት ደንብ ያፀድቃል፣

ሰ) ለጣቢያው ቀጣይነት ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል እንዲሁም ሌሎች በጣቢያው መተዳደሪያ ደንብ የተመለከቱ ተግባር እና ኃላፊነቶችን ያከናውናል፡፡

## 9. የማኅበረሰብ ብሮድካስት ቦርድ አደረጃጀት

1/ ማንኛውም የማኅበረሰብ ብሮድካስት በጠቅላላ ጉባኤው የተመረጡ 7 አባላት ያሉት ቦርድ ሊኖረው ይገባል።

2/ የቦርዱ ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባኤው ነው።

3/ መልክአ ምድራዊ የማኅበረሰብ ብሮድካስት፣ የማኅበረሰብ ተኮር የአካባቢ አስተዳደር ብሮድካስት እና ልዩ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ የቦርድ አባላት ስብጥር፡-

ሀ) ከማኅበረሰቡ የተለያዩ ብዙሃን ማኅበራት፣

ለ) ከአካባቢው ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት፣

ሐ) ከአካባቢው አስተዳደር ምክር ቤት፣ እና

መ) ከሌሎች የጠቅላላ ጉባኤ አባላት የተውጣጣ መሆን ይኖርበታል።

4/ የጋራ ፍላጎት የማኅበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያ የቦርድ አባላት ስብጥር፡-

ሀ) ከአመልካቹ ማኅበር አመራር፣

ለ) ከማኅበሩ አመራር ውጪ ከሆኑ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት፣

ሐ) ከአካባቢው አስተዳደር ምክር ቤት፣ እና

መ) ከአካባቢው ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት የተውጣጣ መሆን ይኖርበታል።

5/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የማኅበረሰብ ብሮድካስት እና የማኅበረሰብ ተኮር የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ብሮድካስት ጣቢያ የቦርድ አባላት ስብጥር፡-

ሀ) ከተማሪዎች ህብረት አመራር አካል፣

ለ) ከከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ ፕሬዝዳንት ወይም አመራር አካል፣

ሐ) ከከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ መምህራንና ሌሎች ሠራተኞች፣ እና

መ) ከአካባቢው አስተዳደር፣ የተለያዩ ማኅበራት እና ሌሎች የጠቅላላ ጉባኤ አባላት የተውጣጣ መሆን ይኖርበታል።

6/ የቦርድ የሥራ ዘመን 3 አመት ይሆናል፤ በየ3 አመቱ የቦርድ አባላት ምርጫ ሲካሄድ የአመራር ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ከነባሩ አባላት መካከል ለጣቢያው ቀጣይነት የሚጥሩ አንድ ሶስተኛ አባላት እንዲቀጥሉ ሊደረግ ይችላል።

7/ የብሮድካስት ጣቢያው ሥራ አስኪያጅ ያለ ድምፅ የቦርዱ ፀሀፊ ሆኖ ይሠራል።

8/ የቦርድ አባላት ለሚሰጡት አገልግሎት ክፍያ ወይም አበል ሳይጠይቁ ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው። ይሁንና በጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀ ስብሰባ በሚያከናውኑበት ቀን አበል ወይም ክፍያ ማግኘት ይችላሉ፡፡

10.<u>የቦርዱ ሥልጣን እና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት መመስረቻ ፅሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ በማዘጋጀት ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ማስፀደቅ፤ ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ጣቢያው ህጋዊ ሰውነት የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

2/ የፈቃድ መስፈርትን በማሟላት ከባለሥልጣኑ ፈቃድ መውሰድ፣

3/ የብሮድካስት ጣቢያው በሚገኝበት አካባቢ ከሚገኙት የአስተዳደር አካላት፣ ማኅበራት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መሥራት፣

4/ የብሮድካስት ጣቢያውን የሚመራ ሥራ አስኪያጅ ወይም ፕሮግራም ኃላፊና የቴክኒክ ኃላፊ በቋሚነት መቅጠር፣

5/ የብሮድካስት ጣቢያውን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ማኅበረሰቡን በበጎ ፈቃደኝነት፣ በፕሮግራም ዝግጅት፣ በገንዘብ ማሰባሰብ እና በጣቢያው ሌሎች ሥራዎች እንዲሳተፍ ግንዛቤውን ማሳደግና ማስተባበር፣

6/ የቦርዱን የስብሰባ፣ የምርጫ፣ የድምፅ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርአት ደንብ ማውጣት፣

7/ የብሮድካስት ጣቢያውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በሚመለከት አመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርት እና በጀት ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ማስፀደቅ እና ሌሎች በመተዳደሪያ ደንብ እና በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡት ኃላፊነቶችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>ስለማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርአት ሂደት</u>

11.<u>አጠቃላይ</u>

1/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ፈቃድ የሚሰጠው የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት በሚመለከተው መንግስታዊ አካል ለተመዘገበ፣ በሕግ የሰውነት መብት ለተሰጠው፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ማኅበር ነው፡፡

2/ ባለሥልጣኑ ከምድር ወደ አየር፣ በሳተላይት ወይም በኬብል አማካኝነት ለሚሰራጭ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አመልካቾች ያለ ውድድር በማንኛውም ጊዜ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም አመልካቹ እንዲሰጠው የሚያመለክተው ፈቃድ የፕሮግራም ትኩረቱን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ አድርጎ ከምድር ወደ አየር የሚሰራጭ ልዩ የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ከሆነ በቅድሚያ ቦርድ ማፅደቅ ወይም በሳተላይትና በኬብል አማካኝነት የሚሰራጭ ከሆነ ባለስልጣኑ ማፅደቅ ይኖርበታል፡፡

4/ ከአንድ በላይ የሆኑ ማኅበረሰቦች በጋራ አንድ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ፈቃድ ማግኘት ይችላሉ።

5/ በአንድ አካባቢ የሚገኙ ከአንድ በላይ የሆኑ አመልካቾች ብቃታቸው ተመጣጣኝ ከሆነ እና የሬዲዮ ሞገድ እጥረት ካጋጠመ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ሞገዱን በጋራ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ይችላል፡፡ ለአፈፃፀም የሚረዳ ዝርዝር አሠራርም ይዘረጋል።

6/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድ ወይም የማስፋፊያ ፈቃድ ሳይሰጠው፡-

ሀ) የሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ፕሮግራም በማዘጋጀት የሳተላይት ብሮድካስት አገልግሎት ስራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

ለ) በታገደ ወይም በተሰረዘ ፈቃድ የብሮድካስት አገልግሎት ማሠራጫ መንገዶችን ተጠቅሞ በማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

ሐ) በአንድ ፈቃድ ከአንድ ማሰራጫ ጣቢያ በላይ ማቋቋም አይችልም፡፡

መ) በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ አንቀጽ 29 ከተዘረዘሩት የብሮድካስት አገልግሎት ማሰራጫ መንገዶች መካከል ቀደም ሲል ፈቃድ ካገኘበት የፈቃድ አይነት ውጪ ከባለሥልጣኑ ሌላ ተጨማሪ ፈቃድ ሳይሰጠው የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡

7/ አንድ ማኅበረሰብ ከአንድ በላይ የማኅበረሰብ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ፈቃድ ማግኘት አይችልም።

8/ በማኅበረሰብ ብሮድካስት የሚሳተፍ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አባላት ኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ይገባል።

9/ የማኅበረሰብ ሬዲዮ የማሰራጫ መሳሪያ ጉልበት ከ1 ኪሎ ዋት መብለጥ የለበትም። ይሁንና ባለሥልጣኑ አመልካቹ የማሰራጫ ጉልበቱን ከ1 ኪሎ ዋት ለማሳደግ ካመለከተ ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው መጨመር ይችላል።

## 12. የማኅበረሰብ ብሮድካስት ፈቃድ አመልካች

የማኅበረሰብ ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ፈቃድ እንዲሰጠው የሚፈልግ አንድ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማህበር በማህበሩ ሕጋዊ ተወካይ አማካኝነት፣ አመልካቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ከሆነም በከፍተኛ ትምህርት ተቋሙ አማካኝነት በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ በመሙላት በማናቸውም ጊዜ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 13. ስለፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ

1/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ ማዘጋጀት ይኖርበታል፣ የማመልከቻ ቅፆችንም በድረ-ገፁ ተደራሽ በማድረግ እንዲሞሉ አማራጭ መንገድ ይፈጥራል፡፡

ሀ) የአመልካቹ ወይም የጣቢያው መጠሪያ ስምና አድራሻ፣

ለ) የብሮድካስት አገልግሎቱ ዓላማ፣ የፕሮግራሙ አይነት፣ የሚሰራጭበት ቋንቋ፣ የሥርጭት ቀን፣ ሰአትና አጠቃላይ ሁኔታ፣

ሐ) ለስርጭቱ የሚውለውን የመሣሪያ አይነትና ጉልበት፣

መ) ለማቋቋም የተጠየቀው የሬዲዮ ሞገድ አይነት፣

ሠ) ስርጭቱ የሚሸፍነው አካባቢ፣

ረ) አገልግሎቱ የሚሰጥበትን፣ የማሰራጫ መሳሪያው የሚተከልበትን ወይም የሚቋቋምበትን ቦታ፣

ሰ) ጣቢያውን ለማቋቋምና አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልገውን የገንዘብና የካፒታል መጠን፣

2/ አመልካቹ ስርጭቱን በሳተላይት አማካኝነት የሚያሰራጭ ከሆነ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) ከተመለከተው በተጨማሪ፡-

ሀ) የሚጠቀምበትን የሳተላይት መጠሪያ ስም፣ የሳተላይት አከራዩ ባለቤት ስም፣ አድራሻ፣ የተደረገ ውልና መሰል መረጃ፣

ለ) አመልካቹ ለስርጭቱ የሚጠቀምበትን የሬዲዮ ሞገድ መጠሪያ ቁጥር፣

ሐ) ሌሎች አገልግሎቱን እና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎችን፡፡

## 14. ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው ስለሚቀርቡ ሰነዶች

አመልካቹ የሚከተሉትን ሰነዶች በማሟላት ከማመልከቻ ቅፁ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

1/ አመልካቹ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት በሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተመዘገበ፣ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ማህበር መሆኑን የሚያስረዳ ሠነድ፣

2/ የአገልግሎትና የቴክኒክ ሁኔታን የሚገልፅ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ፣

3/ ስራውን ለማከናወን የሚያስፈልግ የገንዘብና የካፒታል አቅምና ምንጭ ማስረጃ፣

4/ የጣቢያው ድርጅታዊ መዋቅር ሰነድ፣

5/ የጣቢያውን የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ስም ዝርዝር፣ አድራሻና ፊርማ የያዘ ሠነድ፣

6/ የጣቢያውን ሥራ የሚመሩ ቦርድ አባላትን፣ የሥራ አስኪያጁን፣ የፕሮግራም ኃላፊውንና የሰው ሀይል ሥም ዝርዝር የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ አይነት እና ፊርማ የያዘ ሰነድ፣

7/ የማሰራጫ አንቴና፣ ዲሽ ወይም መሳሪያ የሚገኝበት መልከአምድራዊ መረጃ፣

8/ የብሮድካስት አገልግሎቱ ዓላማ፣ የፕሮግራሙን አይነት፣ የሚሰራጭበት አገራዊ ቋንቋ፣ የሥርጭት ቀን፣ ሰአትና አጠቃላይ ሁኔታ፣ የሚያስረዳ ሰነድ፣

9/ ለማኅበረሰቡ ፍላጎትና ለአገር በቀል ፕሮግራም እና ሙዚቃ የተመደበው የስርጭት ጊዜ መጠን፣

10/ አመልካቹ ስርጭቱን በሳተላይት አማካኝነት የሚያሰራጭ ከሆነ ከላይ ከተመለከተው በተጨማሪ፤ ከሳተላይት አገልግሎት ሰጪው ጋር የተደረገ ማንኛውም አይነት ስምምነት ወይም ደብዳቤና አመልካቹ ለስርጭቱ የሚጠቀምበትን የሬዲዮ ሞገድ መጠሪያ ቁጥር፣

11/ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ብሔረሰቦችን እና በማኅበረሰቡ አባላት የሚነገሩ ቋንቋዎችን አይነትና ብዛት፣

12/ የአመልካቹን ማኅበረሰብ ብዛት የሚያስረዳ ሰነድ፤ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም የማኅበረሰብ ብሮድካስት በስተቀር ከ5,000 በላይ የሆነ የተመዘገበ ማኅበረሰብ ወይም ነዋሪ ያለው መሆን የሚያስረዳ ሰነድ፣

13/ የብሮድካስት ጣቢያው እንዲቋቋምለት የሚጠይቀው ማኅበረሰብ ከ5,000 እስከ 25,000 የሚሆኑ አባላት ያሉት ከሆነ ቢያንስ 300 የሚሆኑ አባላት፣ ከ25,000 እስከ 50,000 የሚሆኑ አባላት ያሉት ከሆነ ቢያንስ 500 የሚሆኑ አባላት፣ ከ50,000 እስከ 100,000 የሚሆኑ አባላት ያሉት ከሆነ ቢያንስ 700 የሚሆኑ አባላት፣ እንዲሁም ከ100,000 በላይ የሚሆኑ አባላት ያሉት ከሆነ ቢያንስ 1,000 የሚሆኑ አባላት በፊርማቸው ያረጋገጡ መሆኑን የሚገልፅ ሰነድ፣

14/ ስለብሮድካስት ጣቢያው መቋቋም ቦርዱ ውሳኔ ያሳለፈበት ቃለ-ጉባዔ፣

15/ አመልካቹ ከሚገኝበት የአካባቢ አስተዳደር የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፤ አመልካቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የማኅበረሰብ ሬዲዮ ከሆነ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋሙ የበላይ አካል የተሰጠ የድጋፍ ደብዳቤ፣ እና

16/ ሌሎች የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎትንና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎች፡፡

## 15.የፈቃድ መስጫ አጠቃላይ መስፈርቶች

1/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ፈቃድ መስጫ መስፈርቶች የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያካትታል፡፡

ሀ) ከብሮድካስት አገልግሎት ቴክኖሎጂ እድገቶች ጋር በተያያዘ ሊሰጥ ከታሰበው አገልግሎት የሚጠበቅ የቴክኒክ ጥራትና አመልካቹ በፕሮጀክት ሀሳበ-ሥራው የዘረዘራቸው መሣሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች አገልግሎቱን ለመስጠት ያላቸው ብቃት፤

ለ) የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት በሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተመዘገበ፣ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ማኅበር መሆኑ፤

ሐ) ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም የማኅበረሰብ ብሮድካስት በስተቀር ከ5,000 በላይ የሆነ የተመዘገበ ማኅበረሰብ ወይም ነዋሪ ያለው መሆኑ፤

መ) አመልካቹ አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው ተስማሚነት፣ ድርጅታዊ ብቃት፤

ሠ) የአመልካቹ የፋይናንስ አቅምና ምንጭ፣ አስተማማኝነትና ሥራውን ለማስኬድ ያለው ዝግጁነት፤

ረ) በአመልካቹ ፕሮጀክት ሀሳበ-ሥራ የተዘረዘሩ የፕሮግራሞች መርሐግብርና በፕሮግራሞቹ የተካተቱ ማኅበራዊ ፍላጎቶች፤ ለአገር በቀል ፕሮግራምና ሙዚቃ የሰጠው ትኩረት፣ እና

ሰ) አመልካቹ ለአገልግሎቱ የመደበው የስርጭት ጊዜ፡፡

2/ በአዋጁ አንቀፅ 32(1) መሰረት ባለሥልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር በማድረግ ተጨማሪ የፈቃድ መስፈርቶችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

3/ የማህበረሰብ ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ጣቢያው የራሱን የባንክ አካውንት መክፈትና ማንቀሳቀስ ይኖርበታል፤ አካውንቱን በመፈረም የሚያንቀሳቅሱ አባላት በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወሰነው መሰረት ይሆናል፡፡

## 16.የፈቃድ መስጫ ዝርዝር መስፈርቶች እና የመገምገሚያ ነጥብ አሰጣጥ ሥነ ሥርአት

1/ የፈቃድ መስጫ ዝርዝር መስፈርቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ለመስጠት በሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተመዘገበ፣ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ማኅበር መሆኑ፤

ለ) ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም የማኅበረሰብ ብሮድካስት በስተቀር ከ5,000 በላይ የሆነ የተመዘገበ ማኅበረሰብ ወይም ነዋሪ ያለው መሆኑ፤

ሐ) አገልግሎቱን ለመስጠት ያለው የፋይናንስ፣ የካፒታል፣ የሰው ሀይልና የድርጅታዊ አቅም፣ ብቃት፣ ዕውቀትና የሥራ ልምድ፣

መ) በፕሮጀክት ሰነዱ የተዘረዘሩትና ለስርጭት የሚውሉት የብሮድካስት መሣሪያዎች አይነት፣ የስቱዲዮ አደረጃጀት፣ የቴክኒክ ደረጃና ብቃት፣

ሠ) አገልግሎቱ የሚሰጥበት ወይም የማሰራጫ መሳሪያ፣ አንቴና ወይም ዲሽ የሚቋቋምበት መልከአ ምድራዊ ቦታ አስተማማኝነት፣

ረ) የብሮድካስት አገልግሎቱ ወይም የፕሮግራሙ አላማ፣ የፕሮግራሙ አይነት፣ የሥርጭት ቀንና ሰአት፣

ሰ) በአመልካቹ የቀረበው የፕሮግራም ይዘት፣ አላማ፣ በፕሮግራሙ የተካተቱ ማህበራዊ ፍላጎቶችና ለትምህርታዊ ፕሮግራሞች የሰጠው ትኩረት፣

ሸ) ፕሮግራሙ ለህፃናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞችና ልዩ ድጋፍ ለሚፈልጉ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሰጠው ትኩረት፣

ቀ) ፕሮግራሙ የሚሰራጭበት አገራዊ ቋንቋ ብዛት፣

በ) ለአገር በቀል ይዘት፣ ፕሮግራምና ሙዚቃ የመደበው የሥርጭት ጊዜ መጠን፣

ተ) የጣቢያው ዕለታዊ የሥርጭት ጊዜ መጠን እና የሚሸፍነው አካባቢ፣

ቸ) ለስርጭቱ የሚውለው የሬዲዮ ሞገድ፣ የሳተላይት አይነት፣ የሳተላይቱ ባለቤት ስም፣ አስተማማኝነትና ለህዝብ የሚኖረው ጠቀሜታ፣

ነ) ከሕብረተሰቡ የቀረበ ተደጋጋሚ ቅሬታና ከባለሥልጣኑ የተሰጠ ተደጋጋሚ የማስተካከያ ግብረመልስ አለመኖሩ፣

ኘ) ሌሎች የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎትንና አመልካቹን አስመልክቶ የሚጠየቁ መረጃዎች፡፡

2/ ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 15 እና 16 የተዘረዘሩትን አጠቃላይና ዝርዝር የፈቃድ መስፈርቶች፣ እንዲሁም የተጠየቀውን የብሮድካስት ፈቃድ አይነት እና የማሰራጫ ቴክኖሎጂን ግምት ውስጥ በማስገባት የአመልካቾችን ብቃት በመመዘን ነጥብ ለመስጠት የሚያስችለውን ዝርዝር መስፈርት እና የመመዘኛ ነጥብ አሰጣጥ ሥነ ሥርአት ሠነድ ያዘጋጃል፣ በባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በማስፀደቅ ስራ ላይ ያውላል፡፡

17.<u>የማኅበረሰብ ብሮድካስት ፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ሂደት</u>

የማኅበረሰብ ብሮድካስት ፈቃድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርአት ሂደት የሚከተለውን የሥራ ፍሰት ጠብቆ ይከናወናል፡-

1/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚፈልግ አመልካች በማናቸውም ጊዜ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ከደጋፊ ሠነዶች ጋር ለባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ያቀርባል፣

2/ የባለሥልጣኑ የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል የቀረበለትን ማመልከቻ በመመርመርና የመጀመሪያ ማጣሪያ በማድረግ፡-

ሀ) አመልካቹ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ካላቀረበ፣ ለትርፍ የተቋቋመ ማኅበር ከሆነ፣ ወይም በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ በአንቀጽ 40 መሠረት ፈቃድ የማይሰጠው አካል መሆኑን ካረጋገጠ፣ ማመልከቻውን በዝርዝር ማጣራት ሳያስፈልገው ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆንና ውሳኔው ለአመልካቹ በጽሁፍ እንዲገለፅለት የውሳኔ ሃሳቡን ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

ለ) አመልካቹ ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ካቀረበና በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ በአንቀጽ 40 መሠረት ፈቃድ ሊሰጠው የሚችል አካል መሆኑን ካረጋገጠ፣ ማኅበረሰቡ ዘንድ በአካል ተገኝቶ ይወያያል፣ በአዋጁ አንቀጽ 37 እና በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 15 እና 16 የተዘረዘሩት የፈቃድ መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥና ለመመዘን ወደ ሁለተኛ ማጣሪያ እንዲያልፍ ውጤቱን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

3/ የበላይ ሃላፊው ከፈቃድ ስራ ክፍሉ የቀረበለትን የአመልካቾች ዝርዝርና የውሳኔ ሃሳብ በመመርመር ወደ ሁለተኛ ማጣርያ ማለፍ የሚገባውን አመልካች በማፅደቅ ምዘናና ግምገማ እንዲካሄድ ይወስናል፡፡

4/ የፈቃድ ስራ ክፍሉ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 የቀረበለት ማመልከቻ በአንቀጽ 14፣ 15፣ እና 16 የተዘረዘሩትን ሰነዶችና መስፈርቶች ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ፣ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 16(2) መሰረት በተዘጋጀው የፈቃድ አሰጣጥ የመመዘኛ ነጥብ አሰጣጥ የአሰራር ሥነ ሥርአት መሰረት የአመልካቹን ብቃት በመመዘንና አመልካቹ ያገኘውን ውጤት የያዘ የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

5/ የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የአመልካቹ ማኅበረሰብ ፍላጎት በሌሎች የብሮድካስት አገልግሎቶች ያልተሸፈነ መሆኑን ያጣራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በቀረበለት የፈቃድ ማመልከቻ ላይ አመልካቹም ሆነ ዜጎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡና ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

6/ የበላይ ኃላፊው በፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብና አስተያየት እንዲሁም በአመልካቹ የቀረበለትን ሠነድ፣ የሕዝባዊ አስተያየቱን ውጤትና ሌላ መረጃ መርምሮ አመልካቹ የፈቃድ መስጫ መስፈርቶችን ማሟላቱን ሲያረጋግጥ ፈቃድ እንዲሰጠው ውሳኔ ይሰጣል፡፡

7/ ባለሥልጣኑ የወሰነውን ውሳኔ፣ ለውሳኔው ያደረሱ ምክንያቶችንና ፈቃድ ሲሰጥ ተግባራዊ የሚሆኑ የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎችን ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፣ እንዲሁም በድረ-ገጹ፣ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌላ የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

8/ አመልካቹ መስፈርቱን አለማሟላቱ ከተረጋገጠ ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኝ በማድረግ መስፈርቱን የሚያሟላበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ መስፈርቱን ለማሟላት ካልቻለም የፈቃድ ማመልከቻው ይሰረዛል፡፡

9/ የፈቃድ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ሁኔታና ግዴታን የያዘ የፈቃድ ስምምነት ሰነድ ከፈረመና ተገቢውን የፈቃድ ክፍያ ከከፈለ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

10/ አመልካቹ የተፈቀደለት የብሮድካስት ፈቃድ የሬዲዮ ሞገድ እና የሊንክ ሬዲዮ ሞገድን የሚጠቀም ከሆነ፣ ለአመልካቹ የሬዲዮ ሞገድ ወይም የሊንክ ሬዲዮ ሞገድ እንዲመደብለትና እንዲሰጠው ባለስልጣኑ ለኮሙዩኒኬሽን አገልግሎቶች ባለሥልጣን በደብዳቤ በማሳወቅ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

11/ የፈቃድ ምስክር ወረቀት እንዲወስድ በጽሑፍ የተገለፀለት አመልካች ደብዳቤ በደረሰው በ2 ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያ በመፈፀም እና በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ሁኔታና ግዴታ ስምምነት ሰነድ በመፈረም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ካልወሰደ የፈቃድ ውሣኔው ይሰረዛል፡፡

12/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (11) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ቢኖርም ባለፈቃዱ የተዘጋጀውን ሰነድ በመፈረም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ያልወሰደው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ ባለሥልጣኑ የ3 ወር ተጨማሪ ጊዜ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

## 18. በፈቃድ አመልካች ላይ ሕዝባዊ አስተያየት ስለመጥራትና አመልካቹን ቃለመጠይቅ ስለመጠየቅ

1/ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብን ማመልከቻ ለመገምገም ሕዝባዊ አስተያየት ማሰባሰብ ከፍ ያለ የሕዝብ ጥቅምን የሚያረጋግጥ ከሆነ፣ ባለስልጣኑ ሕዝባዊ አስተያየት የሚሰጥበትን መድረክ ለመጥራት ሊሟሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች ለይቶ በማውጣት ጣቢያው በሚቋቋምበት ማኅበረሰብ ውስጥ ሕዝባዊ መድረክ ሊጠራ ይችላል፡፡

2/ አመልካቹ ፈቃድ በማግኘት አገልግሎቱን በጥራት ለማከናወን ያለውን ዝግጁነት በተመለከተ የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊዎችና የፈቃድ ስራ ክፍሉ ለሚያቀርቡለት የቃል መጠይቅ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ሊደረግ ይችላል፡፡

## 19. የማኅበረሰብ ብሮድካስት ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመንና ስለፈቃድ እድሳት

1/ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ የማኅበረሰብ ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን አገልግሎት ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን 10 አመት ሲሆን ለአጭር ጊዜ የተሰጠ የማህበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ፈቃድ ከሆነ ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን 1 አመት ይሆናል፡-

2/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ የተወሰነው የፈቃድ ዘመን ከማለቁ ከ1 ዓመት ባልበለጠና ከ6 ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ ያዘጋጀውን የፈቃድ ማሳደሻ ቅጽ ሞልቶ ማመልከቻውን በማቅረብ ፈቃዱን ማሳደስ ይኖርበታል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የታደሰ ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን 1 አመት ሲሆን ፈቃዱም በየአመቱ ይታደሳል፡፡

4/ የባለሥልጣኑ የፈቃድና ምዝገባ ሥራ ክፍል ፈቃዱን ከማደሱ በፊት፡-

ሀ) ባለፈቃዱ የፈቃድ ሁኔታዎችንና ግዴታዎችን፣ በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች የተመለከቱ ግዴታዎች የማክበር የኋላ ታሪክና የተወሰዱበት አስተዳደራዊ እርምጃዎች አለመኖራቸውን ከግምት ውስጥ ማስገባት፣

ለ) ባለፈቃዱ በተገልጋዩ ማኅበረሰብ ተቀባይነትን ያገኘ፣ ተደጋጋሚ የሆነ የቅሬታ ሪከርድ የሌለበት፣ በባለሥልጣኑ የሞኒተሪንግና ክትትል ውጤት ተደጋጋሚ ግድፈት ያልተገኘበት መሆኑን፣

ሐ) የሬዲዮ ሞገዱ ከፍ ላለ የሕዝብ ጥቅም አለመፈለጉን፣

መ) ባለፈቃዱ በፈቃድ ዘመኑ ውስጥ አመታዊ ክፍያውን በወቅቱ ይከፍል የነበረ መሆኑን በማረጋገጥ ለበላይ ኃላፊ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

5/ የበላይ ኃላፊው የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብና መረጃዎች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

6/ የፈቃድ እድሳት ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚውልበት ሁኔታ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ግዴታ የያዘ ስምምነት ሠነድ በመፈረምና ለፈቃድ እድሳት የተተመነውን ክፍያ ከፍሎ የፈቃድ እድሳት አገልግሎት ያገኛል፡፡

## 20.ተቀባይነት ስላላገኘ የፈቃድ ጥያቄ እና የፈቃድ እድሳት ማመልከቻ

1/ ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) በአንቀፅ 17(2)(ሀ)፣ (8) እና (11) መሰረት የፈቃድ ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን ወይም እንዲሰረዝ ከወሰነ፤ ማመልከቻው ውድቅ የሆነበትን ወይም የተሰረዘበትን ምክንያት በ14 ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ፣ ወይም ሰፊ ስርጭት ባለው የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

ለ) ባለሥልጣኑ በአንቀፅ 19 መሰረት ፈቃድ ላለማደስ የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ካመነ ለባለፈቃዱ በፅሁፍ በመግለፅ በ14 ቀናት ጊዜ ውስጥ ባለፈቃዱ አስተያየቱን እንዲሰጥና ቅሬታ ካለው በፅሁፍ እንዲያቀርብ እድል ይሰጣል፡፡ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን ምላሽ በመገምገም የአመልካቹን ፈቃድ የማያድስ ከሆነ ከ3 ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ለባለፈቃዱ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው በበላይ ኃላፊው ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።

3/ ቦርዱም የአመልካቹ አቤቱታ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና የውሳኔውን ቅጂም በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ መስጠት አለበት፡፡

4/ በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡

## 21.<u>የሥርጭት አገልግሎትን ለማስፋፋት የማስፋፊያ ፈቃድ ስለማስፈለጉ</u>

1/ ማንኛውም ባለፈቃድ የሥርጭት አገልግሎቱን ለማስፋት የሚከተሉትን ለውጦች ለማድረግ ሲፈልግ፤ መሳሪያው የሚተከልበትን ቦታ ከአስፈላጊ ዝርዝር መረጃ ጋር ለባለሥልጣኑ ማቅረብ እና በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ የማስፋፊያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

ሀ) የስርጭት አገልግሎት ከሚሰጥበት አካባቢ ውጪ ሌሎች አካባቢዎችን ለማዳረስ፤ ተጨማሪ ስርጭት ለማካሄድ ወይም ተጨማሪ የሬዲዮ ሞገድ ለማግኘት፣

ለ) የማሰራጫ መሣሪያውን ጉልበት ከተፈቀደው መጠን ለመለወጥ፣ ቦታ ለመቀየር፣ የጣቢያውን አቅም ለማሳደግ፣

ሐ) የቴክኖሎጂ ለውጥ ለማድረግ፣ እና

መ) የአንቴናውን ዓይነትና ተሸካሚ ምሰሶውን ርዝመት ወይም ቦታ ለመቀየር፡፡

2/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሰረት የማስፋፊያ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት፡-

ሀ) ፈቃድ በተጠየቀበት አካባቢ የተመዘገበ በቂ የሬዲዮ ሞገድ መኖር አለመኖሩንና የማስፋፊያ ፈቃድ የተጠየቀበት የሬዲዮ ሞገድ በሌላ የብሮድካስት አገልግሎት አለመያዙን ወይም ለሌላ አገልግሎት አለመፈለጉን፣

ለ) የተመረጠው የማስፋፊያ ቦታ ለታቀደው አገልግሎት ተስማሚ መሆኑን፣

ሐ) አገልግሎቱን ለማስፋፋት የቀረቡት መሣሪያዎች ከታቀደው የአገልግሎት ማስፋፊያ ጋር መጣጣማቸውን፣

መ) የሌሎች የመገናኛ አገልግሎት መሣሪያዎችን ሥራ የማያውክ መሆኑን፣ እና

ሠ) ፈቃድ የተጠየቀበትን አካባቢ ኅብረተሰብ ፍላጎትና የሕዝብ ጥያቄን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

## 22.<u>የፈቃድ ሁኔታዎችና ግዴታዎች</u>

1/ ባለሥልጣኑ ለአመልካቹ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት፤ ባለፈቃዱ ፈቃድ ለማግኘት ሲል በማመልከቻው የገለፀውን የፈቃድ ሁኔታ እና ባለፈቃዱ ሊከተለው የሚገባ ግዴታን መሠረት ያደረገ የፈቃድ ስምምነት ሰነድ ያዘጋጃል፤

2/ ያዘጋጀውን የፈቃድ ሁኔታና ግዴታ የሥምምነት ሰነድ አመልካቹ እንዲያገኛቸውና አስተያየቱን የመግለፅ እድል እንዲሰጠው እና የስምምነት ሠነዱን በመፈረም ፈቃድ እንዲሠጠው ያደርጋል፡፡

3/ ባለፈቃዱ ፈቃዱን ለመውሰድ ባመለከተበት ወቅት በማመልከቻው ላይ የገለፀው የፈቃድ ሁኔታና የፈቃድ ስምምነት ሠነድ የፈቃድ ግዴታዎች ሆነው ይቆጠራሉ፡፡

4/ የፈቃዱ ሁኔታዎችና ግዴታዎች እንደ ፈቃዱ አይነት ሊለያዩ የሚችሉ ቢሆንም፣ የሚከተሉትን መሠረታዊ ሁኔታዎች ያካትታል፡-

ሀ) አገልግሎቱ የሚሸፍነውን የፈቃድ ክልል፣

ለ) የቴክኒክ መስፈርቶች መዘርዝር፣

ሐ) ባለፈቃዱ ሥርጭት የሚጀምርበትና ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ፣

መ) የፈቃድ ማደሻ ሁኔታዎች፣

ሠ) የአገልግሎት ክፍያ መጠን፣

ረ) የፕሮግራም ፎርማት ግዴታዎች፣

ሰ) የፕሮግራም የይዘት ደረጃዎች፣

ሸ) የፈቃድ ሁኔታዎች ሲጣሱ ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች፣

ቀ) ባለሥልጣኑ በመደበኛነትና ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጠይቃቸው የመረጃ አይነቶች፣

በ) ፈቃድ የሚሻሻልባቸው ሁኔታዎች፣ እና፣

ተ) ቅሬታዎችና አለመግባባቶች የሚያዙበትና እልባት የሚያገኙበት መንገድ፣ የሚሰጡ መፍትሔዎችና እርምቶች፣

ቸ) ስለ አገልግሎትና የተጠቃሚዎች መብት የሚሰጥ መረጃ ግልፅነት፣

## ክፍል አራት
## የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃድ መብቶች እና ግዴታዎች

### 23.የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃድ መብቶች

1/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃዶች፡-

ሀ) ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

ለ) ተግባራቸውን በብቃት ለመፈጸም በሚያስችላቸው ሁኔታ በይዘት፣ በአደረጃጀታቸውና በበጀታቸው ከመንግሥት አካላት እና ከፖለቲካዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖዎች ነፃ የመሆን መብት አላቸው፡፡

ሐ) ሕገ መንግሥቱን በመፃረር የፕሬስ ነፃነትን የሚያደናቅፍ አሰራር ከተፈፀመበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

መ) ዜና ወይም መረጃን የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት መብት አላቸው፡፡

ሠ) በመረጡት ሕጋዊ መንገድ የመደራጀት መብት አላቸው፡

ረ) በዚህ መመርያ በግልፅ የተመለከቱ መስፈርቶችን በማሟላት ፈቃድ፣ የማስፋፊያ ፈቃድ እና የፈቃድ እድሳት የማግኘት መብት አላቸው፡፡

2/ በሕግ በግልፅ ከተመለከተው አግባብ ውጪ በብሮድካስት ስርጭት ላይ የይዘት ግዴታዎች አይጣሉም፡፡

3/ በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ አንቀፅ 49 ከተመለከተው ውጪ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ለመገናኛ ብዙሃን ማንነቱ እንዳይገለጽ በመስማማት መረጃ የሰጠን ምንጭ እንዲገልጹ አይገደዱም፡፡

4/ ባለስልጣኑ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃዶች መብቶች ተግባራዊነት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፡፡

5/ ባለሥልጣኑ፣ የአካባቢ አስተዳደር፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና፣ የሕዝብ ብሮድካስት ጣቢያዎች በአካባቢ ደረጃ የተቋቋሙ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ጣቢያዎችን ቀጣይነት ለማረጋገጥ እንደአግባብነቱ የበጀት፣ የቁሳቁስ፣ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 24.<u>ፕሮግራም፣ ዜና እና ማስታወቂያን በሕግ አግባብ የማሰራጨት ግዴታ</u>

1/ በማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ኘሮግራም፣ ዜና ወይም ማስታወቂያ የሚከተሉትን ማክበር ይኖርበታል፡-

ሀ) ሕገ መንግስቱን፣ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁን፣ የማስታወቂያ አዋጁን፣ የሙያውን የስነ-ምግባር መመሪያ፣ ለቅጅና ተዛማጅ መብቶች ጥበቃ የወጡ ሕግጋትን እና ሌሎች የአገሪቱን ሕጎች ማክበር፣

ለ) የተለያዩ አመለካከቶችን በማንፀባረቅ አጠቃላይ ሕብረተሰቡን የሚያገለግሉ ሚዛናዊና ከአድልዎ የፀዳ መሆን፣

ሐ) የኘሮግራምና ዜና ይዘትና ምንጭ እውነተኛ፣ ትክክለኛ፣ ፍትሐዊና ከአድልኦ የጸዱ መሆኑን ማረጋገጥ፤ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግና ስህተት ሲገኝም ማረም፡፡

2/ በብሮድካስት አገልግሎት ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ኘሮግራም ወይም ዜና፣

ሀ) የማንኛውንም ሰው የግል ሕይወት የመከበር መብትን የሚጥስ፣

ለ) የሰው ልጆችን ክብር የሚፃረር፣

ሐ) ለጤናና ለደኅንነት ጎጂ የሆነ ባህሪን የሚያበረታታ፣

መ) የወንጀል ድርጊት እንዲፈጸም፣ ሰላምና ፀጥታ እንዲደፈርስ የሚቀሰቅስ፣

ሠ) ማንኛውም የሰው ዘርን፣ ቋንቋን፣ ዜግነትን፣ ብሔርን፣ ቀለምን፣ ኃይማኖትን፣ ሥርአተ ጾታን፣ እድሜን ወይም የአእምሮ በሽታንና የአካል መጉደልን መሰረት በማድረግ እንዲጠላ፣ ጥቃት እንዲደርስበት ወይም እንዲገለል የሚቀሰቅስ፣ መሆን የለበትም፡፡

3/ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አልኮል፣ አደንዛዥ ዕፅ፣ ጥቃት ወይም ሌላ አሰቃቂ ወይም አስደንጋጭ ሁኔታዎችን የሚዘግቡ ዜና ወይም ፕሮግራሞችን ሲያሠራጭ በአቀራረባቸው ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4/ ፕሮግራምና ዜና በጣቢያው ከመሠራጨቱ በፊት ሕግን የሚያከብር መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

5/ ባለፈቃዱ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን አመለካከትና ስነልቦና ሊጎዳ የሚችል ፕሮግራምን ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ንጋቱ 11 ሰዓት ካለው ሰዓት ውጪ ማስተላለፍ የለበትም፡፡

6/ የኃይማኖት ተኮር ፕሮግራሞችን የሚያሰራጭ ባለፈቃድ በኃይማኖቶች ተከታዮች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት ማነሳሳት፣ የሌሎችን ኃይማኖት ወይም እምነት ማንኳሰስ፣ ወይም በኃይማኖቶች ተከታዮች መካከል አለመቻቻል እንዲፈጠር መቀስቀስ የለበትም፡፡

## 25.<u>የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ይዘት ተኮር ግዴታዎች</u>

በአዋጁ አንቀፅ 31 (2) መሠረት ትኩረቱን በአንድ ጉዳይ ላይ አድርጎ እንዲዘግብ የተፈቀደለት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1/ በአካቢው የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የባህል፣ የቋንቋ፣ የሃሳብ ብዝሃነት፣ ፍላጎት፣ እይታና ስሜት የሚያንጸባርቁና የሚያስተናግዱ መረጃ ሰጪ፣ አስተማሪና አዝናኝ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

2/ በአካቢው ለሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች የባህልና ቋንቋ ፍትሃዊ ሽፋን የመስጠት፣ የማኅበረሰቡን ቋንቋ፣ ባህልና ጥበባዊ እሴቶች የማስተዋወቅና የማጎልበት፤

3/ ለአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ብልፅግና፣ እንዲሁም በሕገ መንግሥቱና በሌሎች የሕዝብ ጥቅምና የጋራ አገራዊ እሴቶች እንዲጠናከሩ አስተዋፅኦ የሚያደርግ የብሮድካስት አገልግሎት የመስጠት፤

4/ የማኅበረሰቡን ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መሠረቶች የሚጠብቁ፣ የሚያጠናክሩና የሚያሳድጉ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

5/ በዕለቱ ፕሮግራም ውስጥ አካባቢያዊ፣ ክልላዊና አገራዊ ዜናዎችንና መረጃን በትክክልና ከአድልኦ በጸዳ መልኩ የመሰብሰብና የማቅረብ፤

6/ በፕሮግራም ሥርጭቱ ተገቢና ጨዋ የቋንቋ አጠቃቀም ተግባራዊ የማድረግ፤

7/ በፕሮግራም መርሀ-ግብሩ መሰረት ፕሮግራሞችን የማሠራጨት፤ በመርሀ ግብሩ መሠረት ማሠራጨት ካልተቻለ አስቀድሞ የማሳወቅ፤

8/ በፕሮግራሞች ውስጥ አካባቢያዊ ባህልና ቋንቋዎችን ማበረታታትና ሕብረ-ብሔራዊ ማንነት መጎልበቱንና መጠበቁን የማረጋገጥ፤

9/ ለሕፃናት፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች በተለየ ሁኔታ የተዘጋጁ የፕሮግራም ይዘቶችን የማሰራጨት፤

10/ በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ሕዝባዊ ተሳትፎና የሰላ ክርክር የሚደረግበትን መድረክ የማመቻቸት፤ እና

11/ በአጠቃላይ የብሮድካስት አገልግሎቶች ይዘት ዴሞክራሲያዊ፣ ራሱን የቻለ፣ በመረጃ የበለጸገ፣ አዲስ ነገር ለመቀበል ዝግጁ የሆነ፣ ሳይንሳዊ፣ ፈጠራን የሚያበረታታ፣ ቻይና ታጋሽ የሆነ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር የሚያበረታቱና በሃገር ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን፣ ሃገራዊ ልምዶችንና መዳረሻ ግቦችን የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን የማረጋገጥ፡፡

12/ ተደራሽነትንና ውድድርን ለማበረታታት በቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች ባለፈቃዶች ጋር መተባበር ይኖርበታል፡፡

13/ ሌሎች የብሮድካስት አገልግሎቶች ሊያሠራጩ ያልቻሉትን የማኅበረሰቡን የጋራ ጉዳዩች የሚመለከቱ ኘሮግራሞችን የማሠራጨት፤

14/ ለማኅበረሰቡ ጠቀሜታ ያላቸውና ማኅበረሰቡን መሠረት ያደረጉ አስፈላጊ መረጃዎችንና የመዝናኛ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የማኅበረሰቡን የመረጃ አጠቃቀም ባህልና እውቀት የማዳበር፤

15/ በተለይ ለድሆችና ለተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተለየ ስጋት የፈጠሩ ከማኅበረሰብ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው የሰብዓዊ መብት፣ የልማት፣ የጤና አጠባበቅ፣ የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽሉ፣ የትምህርትና የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ላይ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

16/ የማኅበረሰቡን ዴሞክራሲያዊ ባህልን የሚያጎለብቱ፣ ባህሉን የሚያበለጽጉና በነዋሪዎቹ መካከል የጋራ ስሜት እንደ አግባብነቱም ሀገራዊ ሥነ-ምግባር የሚፈጥሩ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤

17/ የማኅበረሰቡን ሁለንተናዊ እድገት በሚመለከት የውይይት መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣

18/ በቴሌቪዥን በቀጥታ ሥርጭት የሚሠራጩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ፕሮግራሞችን ሲያቀርብ የፕሮግራሙን ይዘት በምልክት ቋንቋ የማቅረብ፤ እና፣

19/ በቴሌቪዥን በጽሁፍ የሚያቀርባቸውን አስፈላጊ መረጃዎች በድምጽ አስደግፎ የማቅረብ፡፡

20/ በባለስልጣኑ አስቀድሞ ፈቃድ ሳያገኝ በሌላ የአገር ውስጥም ሆነ በውጪ መገናኛ ብዙሃን የሚሰራጭ ፕሮግራምን ሊንክ አድርጎ ማቅረብ አይችልም፡፡

21/ በቀጥታ ስርጭት የሚተላለፍ ወሳኝ አገራዊ ጉዳዮች ሲኖሩ ከጣቢያው ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሰረት በቀጥታ ሊንክ ማሰራጨት ይችላል፡፡

## 26. <u>የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃዱ አስተዳደራዊ ግዴታዎች</u>

የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ ተግባር፣ ሃላፊነቶች መከናወናቸውን ያረጋግጣል፡-

1/ በፕሮግራም ዝግጅት በጎፈቃደኞችን እና የማኅበረሰቡን አባላት የማሣተፍ፤

2/ ከእርዳታ፣ ከስጦታ፣ ከድጋፍ፣ ከማስታወቂያ፣ ከአባላት መዋጮና ከተለያዩ ሕጋዊ ምንጮች የሚገኙ ገቢዎችን ለማሠራጫ ጣቢያው አገልግሎት የማዋል፤

3/ በሳምንት ቢያንስ ለ14 ሰዓታት የፕሮግራም ስርጭት የማካሄድ፣

4/ ለሚያስመጣቸው መሳሪያዎች በቅድሚያ ከባለሥልጣኑ የማረጋገጫ ሠርተፍኬት የማግኘት፣

5/ የተመደበለትን የሬዲዮ ሞገድ ለሌላ አላማ ያለማዋል፡፡

6/ በእያንዳንዱ ፕሮግራም መጀመሪያና መጨረሻ ላይ የጣቢያውን ስያሜ፣ ምልክት እና ፕሮግራሙ የተላለፈበትን ቀንና የፕሮግራሙን ኃላፊና አዘጋጅ ስም መግለጽ ይኖርበታል፡፡

7/ ቋሚ የፕሮግራም ሀላፊ መመደብና ለሚያሠራጨው ፕሮግራም እና ዜና ኃላፊ አድርጎ የሚመድበውን ሰውና የሃላፊነት ድርሻውን ለባለስልጣኑ ማሳወቅ፤

8/ በፈቃዱ ላይ በተመለከተው የፕሮግራም "ቻናል" ብቻ ፕሮግራሙን የማሠራጨት፤

9/ ማስታወቂያንና ዜናን ጨምሮ ያሰራጨውን ማናቸውም ፕሮግራም ለ30 ቀናት ቀርጾ የማስቀመጥ፤ የተላለፈው ፕሮግራም ላይ ቅሬታ ከቀረበም ባለፈቃዱ

ቅሬታው ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ ፕሮግራሙን ይዞ ማቆየትና በባለስልጣኑ ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ለቁጥጥር ወይም የቀረበ ቅሬታን ለመመርመር ሲጠየቅም ቅጂውን በራሱ ወጪ ማቅረብ ይኖርበታል፤

10/ የጣቢያውን ወጪና ገቢ ኦዲት ማስደረግ፤

11/ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ተባባሪ ፕሮግራም አዘጋጆች የብቃት ማረጋገጫና የንግድ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ

ይኖርበታል፡፡

## 27.<u>አገር በቀል ፕሮግራም እና ሙዚቃ የማሠራጨት ግዴታ</u>

1/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በዕለቱ ፕሮግራም ውስጥ በከፍተኛ መጠን ሀገራዊ ይዘት ያላቸውን ፕሮግራሞችን ማቅረብና ከአካባቢው ማኅበረሰብ የሚመነጩና በአካባቢው ማኅበረሰብ ቋንቋ የሚዘጋጁ ፕሮግራሞችን ማበረታታት ይኖርበታል፡፡

2/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃድ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ጥቅም ለሚያረጋግጡ አገር በቀል ይዘቶች ሰፊ ትኩረት የሚሰጡ ይዘቶችን በማዘጋጀት ማቅረብ የሚኖርበት በመሆኑ፡-

ሀ) አገር አቀፍ ሥርጭት ያለው የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ ሥርጭት ጊዜው 80 በመቶውን ማኅበረሰቡን ለሚመለከቱ ሀገር በቀል ፕሮግራሞች፣ 20 በመቶውን የሥርጭት ጊዜ ለክልላዊ፣ አካባቢያዊ እና ሌሎች ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

ለ) ክልላዊ ሥርጭት ያለው የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ የሥርጭት ጊዜው 70 በመቶውን የክልሉን ማኅበረሰብ ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች፣ 30 በመቶውን የሥርጭት ጊዜ ለአገራዊ፣ አካባቢያዊ እና ሌሎች አገር በቀል ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

ሐ) ማንኛውም አካባቢያዊ ሥርጭት ያለው የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ የሥርጭት ጊዜው 70 በመቶውን የአካባቢውን ማኅበረሰብ ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች፣ ቀሪውን የሥርጭት ጊዜ ለአገራዊ፣ ክልላዊ እና ሌሎች አገር በቀል ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

3/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃድ ከሳምንታዊ የሙዚቃ ሥርጭት ጊዜው ቢያንስ 80 በመቶውን በአካባቢው የኅብረተሰብ ክፍሎች ለተደረሱና ለተቀናበሩ ዜማዎችና ለአገራችን ሙዚቃዎች ማዋል አለበት፡፡

4/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃድ ከአመታዊ የሥርጭት ጊዜው እስከ 10 በመቶውን ከባለፈቃዱ ገለልተኛ በሆኑ ይዘት አመንጪዎች ለሚዘጋጅ ሃገር በቀል ፕሮግራሞች፣ ሙዚቃዎች፣ ድራማዎች ወይም ዘጋቢ ፊልሞች ዝግጅት ማዋል ይኖርበታል፡፡

5/ ባለስልጣኑም አፈፃፀሙን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

28.<u>ቋንቋ</u>

የማኅበረሰብ ብሮድካስት በሚቋቋምበት አካባቢ ከአንድ በላይ ቋንቋ የሚነገር ከሆነ ፕሮግራም የሚሰራጭበት ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች በተቻለ መጠን የሁሉንም ማኅበረሰብ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

29.<u>ለውጦችን ስለማሳወቅና ስለማስፈቀድ</u>

1/ የማኅበረሰብ ብሮድካስተሩ የሚከተሉትን ለውጦች ባደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ለውጡን ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የሥርጭት አገልግሎቱ ሲጀመር፤

ለ) የሥርጭት አገልግሎቱ ለ1 ወር ሲቋረጥ፤

ሐ) የፕሮግራም መርሀ ግብርና የሥርጭት ሰዓት ለውጥ ሲያደርግ፤

መ) የጣቢያው ስም፣ ምልክትና አድራሻ ላይ ለውጥ ሲያደርግ፤

ሠ) የጣቢያው የጠቅላላ ጉባኤ፣ የቦርድ አባል፣ ሥራ አስኪያጅ ወይም የፕሮግራም ኃላፊ ሲለውጥ፤

ረ) ፈቃድ ለመውሰድ ባቀረባቸው ወይም በተፈቀደለት የብሮድካስት የማሠራጫ መሣሪያ አይነት ወይም ሌሎች ጉዳዮችና መረጃዎች ላይ ለውጥ ሲያደርግ፣

2/ ባለሥልጣኑ የተደረገው ለውጥ በሕግ አግባብ መከናወኑን ይገመግማል፡፡

3/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ለውጦች ከማድረጉ በፊት ለባለሥልጣኑ በፅሁፍ ማሳወቅና ፈቃድ ማግኘት አለበት፡-

ሀ) የሬዲዮ ሞገድ፣ የአንቴናና የማሰራጫ መሣሪያ በተመለከተ ለውጥ ለማድረግና ቦታ ለመቀየር ሲፈልግ፣

ለ) የማሰራጫ መሳሪያ ጉልበት ከአንድ ኪሎ ዋት ለማሳደግ ሲፈልግ፣

ሐ) የውጭ አገር ወይም የአገር ውስጥ ብሮድካስተሮች የሚያስተላልፉትን ዜና ወይም ፕሮግራም ተቀብሎ በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ለማሰራጨት ሲፈልግ፣

መ) ከሳተላይት ድርጅቶች ጋር ያደረገውን ስምምነት ለማሻሻል፣ ወይም ለማቋረጥና ፈቃድ ካገኘበት ሳተላይትና ሬዲዮ ሞገድ ውጪ በሌላ ሳተላይትና ሬዲዮ ሞገድ የብሮድካስት ፕሮግራሞችን ለማሰራጨት ሲፈልግ፣

4/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3(ሐ) መሰረት የውጭ አገር ፕሮግራሙ የሚሰራጭለት አካል የፕሮግራም ዝግጅት የብቃት ማረጋገጫና የንግድ ፈቃድ ማውጣታቸውን እና መስፈርቱን ማሟላታቸውን አረጋግጦ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

## 30.አመታዊ ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ስለማቅረብ

1/ ባለፈቃዱ የጣቢያውን የሥራ አመራርና ሠራተኞች፣ ተባባሪ አዘጋጆች፣ ዓመታዊ የበጀት እቅዶች፣ የሂሣብ መዝገብና ዓመታዊ የስራና የሒሳብ ሪፖርት በተመለከተ መረጃ የመያዝ፣ በባለሥልጣኑ ሲጠየቅም ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የሚከተሉትን ሪፖርቶች የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

ሀ) የድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያመለክት የሥራ ክንውን ሪፖርት፣

ለ) የጣቢያውን የገንዘብና የአይነት እርዳታ እንዲሁም የለጋሾች ዝርዝር ወይም ሌላ የፋይናንስ ምንጭ ማስረጃ እና ዓመታዊ የወጪና ገቢ ሪፖርት፣ የኦዲት ሪፖርት፡፡

ሐ) በፕሮግራም ዝግጅት የሚሳተፉ የበጎ ፈቃደኞች ወይም ሠራተኞች ዝርዝር።

መ) የተባባሪ የፕሮግራም አቅራቢዎች ተገቢ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ የስም ዝርዝርና የሚያሠራጩትን የፕሮግራም ዓይነትና ተዛማጅ ማስረጃዎች፡፡

3/ የማህበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃዱ ከውጭ የተገኘን ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት ከውጭ አገር በእርዳታ ወይም በስጦታ መልክ ከመቀበሉ በፊት በቅድሚያ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ ማስፈቀድ አለበት፡፡

4/ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን መረጃና ሪፖርት ባግባቡና በጥንቃቄ ሥራ ላይ ያውላል፡፡

## 31.የጣቢያውን ኤዲቶሪያል መመሪያ ስለማውጣትና ተግባር ላይ ስለማዋል

1/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ሕገ መንግስቱን፣ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁን፣ የሙያውን ሥነ-ምግባር መሰረት ያደረገ ጣቢያው የሚመራበትን የኤዲቶሪያል ፖሊሲ ወይም መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ኤዲቶሪያል መመሪያውንም ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

2/ በኢዲቶሪያል መመሪያ ውስጥ አገራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ የልማት፣ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር አቅጣጫዎችን በማካተትና የአገሪቱን ሕጎችና ሙያዊ ሥነ-ምግባር መሠረታዊ መርሆችን በመከተል ተግባርና ኃላፊነቱን በብቃት መወጣት ይጠበቅበታል፡፡

## 32.እርማት ወይም መልስ የመስጠት ግዴታ

1/ በማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት በተላለፈ ፕሮግራም መብቴ ተነክቷል ወይም ፕሮግራሙ በአግባቡ አልቀረበም በማለት ቅሬታውን ለጣቢያው የሚያቀርብ ሰው ሲኖር፤ ባለፈቃዱ የቅሬታ አቅራቢውን መብት ሊያከብርለት እና ለጣቢያው የሚያቀርበውን እርማት በፅሁፍ በደረሰው በ5 ቀናት ውስጥ በተመጣጣኝና በተመሳሳይ የአየር ጊዜ ያለ ክፍያ ሊያስተላልፍለት ይገባል፡፡

2/ ጣቢያው እርማቱን ለማስተላለፍ ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ካመነበትም ከ3 ሳምንት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ እርማቱን ማስተላለፍ ያለበት ሲሆን የዘገየበትን ምክንያትም በስልክ ወይም በደብዳቤ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት።

3/ እርማት የማውጣት ወይም መልስ የመስጠት መብቱን የተነፈገ ሰው ጣቢያው ተገዶ መልሱን እንዲያወጣለት ለፍርድ ቤት ወይም ለባለሥልጣኑ ወይም ለመገናኛ ብዙሃን ካውንስል ማመልከት ይችላል፡፡

4/ ባለፈቃዱ በሚያሠራጨው ኘሮግራም ወይም ዜና ስህተት ሲገኝ ለማረም የሚያስችለውን የአሰራር ሥነ-ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

33. <u>ጥቆማ፣ ቅሬታንና ግብረ መልስን ስለማስተናገድ</u>

1/ ባለፈቃዱ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥነ ሥርዓት በመዘርጋት ከአድማጭ ወይም ተመልካቾች የሚቀርብ ጥቆማ እና ቅሬታን ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል፡፡

2/ ባለፈቃዱ ከባለሥልጣኑ ለሚቀርብለት ግብረ መልስ ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የወሰደውን ማስተካከያ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3/ ባለፈቃዱ በየ6 ወሩ የጥቆማ እና ቅሬታ አቅራቢዎችን ስም፣ አድራሻ፣ የቀረቡለትን ጥቆማና ቅሬታዎች ብዛት፣ ምክንያት፣ ለጥቆማው ወይም ለቅሬታው የሰጠውን ምላሽና መሰል መረጃ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

4/ ባለፈቃዱ ከሚሰጠው የብሮድካስት አገልግሎት ጋር በተያያዘ በማናቸውም ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት ከተወሰነበት የአቤቱታውን ብዛት፣ ምክንያት፣ የተሰጠውን ውሳኔና መሰል መረጃ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

5/ ባለስልጣኑ ባለፈቃዶች የራሳቸውን የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት ተከትለው መስራታቸውን ይቆጣጠራል፡፡

34. <u>የብሮድካስት አገልግሎት ክፍያዎችን ስለመክፈል</u>

1/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃድ ከዚህ በታች በተመለከተው ጊዜ መሰረት የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ፣ የፈቃድ ክፍያ፣ አመታዊ ክፍያ ወይም የሬዲዮ ሞገድ ክፍያ እና የፈቃድ ማደሻ ክፍያ ይከፍላል፡፡

ሀ) የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ አመልካቹ የፈቃድ ማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ሲያቀርብ ይከፍላል፡፡

ለ) የፈቃድ ክፍያ አመልካቹ የፈቃድ ምስክር ወረቀት ከመውሰዱ በፊት ይከፍላል፡፡

ሐ) ዓመታዊ ክፍያ እና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ ይከፍላል፡፡

2/ ባለፈቃዱ የመንግስት በጀት አመት በተጠናቀቀ በ60 ቀናት ውስጥ አመታዊና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያውን ካልከፈለ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ወር 5 በመቶ መቀጫ

እየታከለበት ይከፍላል፡፡ ሆኖም የመቀጫው ጠቅላላ ድምር ከዋናው ክፍያ 50 በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ የሚፈለግበትን አመታዊና የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያውን አጠቃሎ ከከፈለ ባለስልጣኑ መቀጫውን ሊያነሳለት ይችላል፡፡

4/ የክፍያው መጠን በመንግስት በሚጸድቀው ተመን መሰረት የሚወሰን ሲሆን፤ ክፍያው በባለስልጣኑ በየጊዜው እየተጠና በመንግስት ይወሰናል፡፡

## 35. <u>ቁጥጥር እንዲደረግ ስለመፍቀድ</u>

1/ ባለሥልጣኑ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጡት ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ኢንስፔክተሮችን ይመድባል፡፡

2/ ኢንስፔክተሩ ቁጥጥር ወደ ሚያደርግበት ጣቢያ ለመግባት የመታወቂያ ወረቀቱን እና ከባለሥልጣኑ ቁጥጥር እንዲያደርግ የተጻፈለትን ደብዳቤ በመያዝ በስራ ሰአት ለመግባትና ቁጥጥር ለማድረግ ይችላል፡፡

3/ ለክትትል እና ቁጥጥር ያመች ዘንድ የሕዝብ ብሮድካስት ባለፈቃዱ የሥራ ቦታውን እና የማሰራጫ ጣቢያውን ክፍት ያደርጋል፤ በኢንስፔክተሩ የሚጠየቀውን የሰነድ ቅጅም ያቀርባል፤

4/ ኢንስፔክተሩ ቁጥጥር ሲያደርግ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃዱ መታደሱን፣ አግባብ ያላቸውን ሰነዶችና የፕሮግራም ቅጅዎች መያዛቸውን፣ የአዋጁና የመመሪው ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለማየትና ቅጅ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል፡፡

## 36. <u>ፈቃድ ስለማስተላለፍ</u>

1/ ባለፈቃዱ ሥራውን ማካሄድ ካልቻለ ፈቃዱን በመመለስ ለባለሥልጣኑ በማመልከት ሲፈቀድለት መሣሪያውን ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ይችላል፡፡

2/ ባለፈቃዱ አስቀድሞ ከባለሥልጣኑ በፅሁፍ ካልተፈቀደለት በስተቀር ፈቃዱን ወይም በፈቃዱ የተሠጡትን መብቶችና የፈቃድ ሁኔታው ላይ ተለይተው የተቀመጡ ጉዳዮችን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይችልም፡፡

# ክፍል አምስት
# ስለአስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃዎች

## 37. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1/ የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃዱ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅንና አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ከተላለፈ በመገናኛ ብዙሃን አዋጁ በተመለከተው መሰረት ባለስልጣኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በየደረጃው ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ለ) እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት መጣል፤

ሐ) ጥሰት የተፈፀመበትን ፕሮግራም ማገድ ወይም መሰረዝ፤

መ) የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድን ማገድ ወይም መሰረዝ፤

2/ ባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሲወስን፡-

ሀ) ጣቢያው አስተዳደራዊ እርምጃ ሊጣልበት እንደሆነና ጥፏል የተባለውን ጉዳይ እንዲያውቅ ማድረግና አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፤

ለ) እርምጃው የሚወሰድበትን ምክንያት፣ የማስተካከያ እርምጃውን፣ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን እና የጊዜ ገደብ በፅሁፍ ለባለፈቃዱ ማሳወቅና አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፡፡

ሐ) የጣቢያውን አጠቃላይ የገንዘብ ሁኔታ፣ በጥፋቱ ምክንያት ያገኘውን የገንዘብ ጥቅም፣ ሕግና መመሪዎችን የማክበር እና ግድፈቶችን የመፈጸም የኋላ ታሪክ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት፤ የገንዘብ ቅጣቱ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3/ ፕሮግራሙ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባለው 6 ወር ጊዜ ውስጥ በፕሮግራሙ ላይ ምርመራ ካልተጀመረ አስተዳደራዊ እርምጃው በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

## 38. አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመወሰን ስልጣን እና ይግባኝ አቀራረብ

1/ የፈቃድ እድሳትን የመከልከል፣ ፈቃድን የማገድ እና ፈቃድን የመሰረዝ አስተዳደራዊ እርምጃዎች የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ቦርድ ይሆናል፡፡

2/ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ የገንዘብ ቅጣት የመጣል እና አንድን ፕሮግራም የማገድ ወይም የመሠረዝ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

3/ ባለሥልጣኑ በወሰነው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለፈቃድ ውሳኔው በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ቦርዱ አቤቱታው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

4/ ቦርዱ በወሰነው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ባለፈቃድ ውሳኔው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

5/ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርዱ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## 39.<u>በፍርድ ቤት የሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

የማኅበረሰብ ብሮድካስት ባለፈቃዱ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅን ከተላለፈ በመገናኛ ብዙሃን አዋጁ በተመለከተው መሰረት በፍርድ ቤት የሚከተሉት ሕጋዊ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ፡-

1/ የስም ማጥፋት ተግባር በመገናኛ ብዙሀን ሲፈፀም በፍትሐብሔር ሀላፊነት እስከ 300,000 ብር (ሦስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የህሊና ጉዳት ካሳ ሊያስቀጣ ይችላል፡፡

2/ ዓቃቤ ሕጉ በብሔራዊ ደኅንነት ላይ ከስርጭት በኋላ በማስቀጣት ሊቀለበስ የማይችል ግልጽና ድርስ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል የብሮድካስት አገልግሎት ሊሰራጭ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው የብሮድካስት አገልግሎቱ እንዳይሰራጭ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ወይም ከነገሩ አጣዳፊነት የተነሳ ጉዳቱን ለመከላከል የፍርድ ቤት የማገጃ ትእዛዝ በፍጥነት ማግኘት ባልቻለ ጊዜ በፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ውሳኔ የብሮድካስት አገልግሎት ሥርጭት እንዲታገድ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3/ የወንጀል ክስ ሲቀርብ ጥሰት የተፈፀመበትን ፕሮግራም ማገድ ወይም መሰረዝ፡፡

4/ የወንጀል ክስ ሲቀርብ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድን ማገድ ወይም መሰረዝ፡፡

# ክፍል ስድስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 40.የባለድርሻ አካላት ተግባርና ሀላፊነት

1/ የማህበረሰብ ሬዲዮ በተቋቋመበት አካባቢ የሚገኝ የአካባቢ አስተዳደር፡-

ሀ) ጣቢያው ለማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ድጋፍ ይሰጣል፣

ለ) ማህበረሰቡ የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራተጂዎች እንዲሁም እቅድ እና አሰራሮችን እንዲገነዘብ እና ለተፈጻሚነታቸውም የነቃ ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች የሚዘጋጁበትን ስልት ከሬዲዮ ጣቢያው ጋር በመተባበር በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ሐ) ከጣቢያው ጋር የተያያዙ ችግሮችና ጣልቃ ገብነቶች ሲከሰቱ እንዲፈቱ ጥረት ያደርጋል፡፡ ከአቅም በላይ ሲሆን ለባለስልጣኑ ያሳውቃል፣

መ) ከጣቢያው ቦርድ ጋር በመመካከር ያጣቢያውን ቀጣይነት ለማረጋገጥ፣ በበጀት ለመደገፍ ወይም አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችለውን ስልት በመቀየስ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

2/ የማህበረሰብ ሬዲዮ በተቋቋመበት አካባቢ የሚገኝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፡-

ሀ) የማህበረሰብ ሬዲዮን ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የበጀት፣ የሰው ሀይል እና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ለ) የኮሚኒቲ አገልግሎትን ለማጠናከር ለማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያው አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ (1) ለአካባቢው አስተዳደር የተሰጡትን ተግባርና ሀላፊነቶች እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

3/ ባለስልጣኑ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ) የማህበረሰብ ብሮድካስተሮች የቴክኒክ ብልሽት ሲያጋጥማቸው ባለሙያ በመመደብ እንዲጠገን ይደግፈል፡፡

ለ) የማህበረሰብ ብሮድካስተሮች የማህበረሰብ ብሮድካስት ዕቃዎችን የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ሐ) ለማህበረሰብ ብሮድካስት ቦርድና ጋዜጠኞች የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፤

መ) በህዝብና በክልል ብሮድካስተሮች የተሰራጩ ፕሮግራሞችን የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፤

ሠ) በፖሊሲ የጸደቁ ድጋፍና ማበረታቻዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

ረ) የማህበረሰብ ብሮድካስተሮች የርስ በርስ ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ስልት ይቀይሳል፤

## 41. መረጃን ተደራሽ ስለማድረግ

ባለሥልጣኑ፡-

1/ መገናኛ ብዙሃን ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች በቀላሉና በቀጥታ ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ሠጪውን ስም፣ አድራሻ፤ የፖስታና የስልክ ቁጥር፣ የኢሜልና የድረ-ገፅ አድራሻ፣ የጣቢያውን ስራ አስኪያጅና ተወካዮች ስምና ስልክ ቁጥር በማጠናቀርና በመመዝገብ በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ ተደራሽ ያደርጋል፡-

2/ በቦርዱ የፀደቁ መመሪያዎችን አሳትሞ ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋል፡፡

## 42. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሕግ መሰረት የተሰጡ የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ፈቃዶች እንደፀኑ የሚቆዩ ሲሆን፤ እንደአስፈላጊነቱ በአዋጁ አንቀፅ 44 እና 88 መሠረት ባለፈቃዶች አደረጃጀታቸውን በማሻሻል የማኅበረሰብ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ፈቃድ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድን ለማሻሻል ሲወስን የሚከተሉትን መረጃዎች ለባለፈቃዱ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የማሻሻያውን ዝርዝር፤

ለ) ለማሻሻል ያስፈለገበትን ዝርዝር ምክንያት፤ እና፣

ሐ) ማሻሻያው ከመቼ ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚደረግ፡፡

## 43. ስለ በጎ ፈቃደኞች

ጣቢያው የማህበረሰብ ብሮድካስት በጎ ፈቃደኛ ጋዜጠኞችን በክፍያ ማሰራት ይችላል፡፡ የትራንስፖርት እና መሰል ወጪያቸውን ጣቢያው ይሸፍናል፡፡

## 44. የተሻረ መመሪያ

1/ የማኅበረሰብ ሬዲዮ መመሪያ ቁጥር 04/2004 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ትእዛዝ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 45. መመሪያውን ስለማሻሻል

የባለሥልጣኑ ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል::

## 46. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጳጉሜ 3 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጳጉሜ 3 ቀን 2014 ዓ.ም**

**የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ቦርድ**